# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የቃል አገልጋዮችና የሽማግሌዎች ስብሰባ

የቃል አገልጋዮችን የሽማግሌዎች ስብሰባ በወንድም ረድኤቱ ቤት የፊታችን ቅዳሜ (Jan. 20, 2018) ከጠዋት 10 a.m. ጀምሮ ይካሄዳል።

### የጌታ እራት

የጌታ እራት ፕሮግራም በፊታችን እሁድ (Jan. 21) በሚኖረን ፕሮግራም ላይ እንካፈላለን። ይህንን ፕሮግራም እያሰብንና እየጸለይን እንድንቀይ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም ዘወትር አርብ ከ7 p.m. ጀምሮ እየተገናኘን እንጸልያለን። ቃሉንም እንማራለን። በዚህ ፕሮግራም ላይ በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንድንሆን ሁላችንም እንድንሳተፍ ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። በተለያየ ጉዳይ እንዲጸለይላችሁ የምትሹም አገልጋዮችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ!

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**


ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)


### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10



## "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?"

(ሮሜ. 8፡31)


Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625



### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.


**January 14, 2018** | **ጥር 6፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ጌቱ ጳውሎስ |
| አምልኮ....................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጌቱ ጳውሎስ |
| ቃል ............. | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

*“በላባዎቹ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም በታች*
*ትተማመናለህ፤ እውነት እንደ ጋሻ*
*ይከብብሃል።*
*ከሌሊት ግርማ፥ በቀን ከሚበርር ፍላጻ፥*
*በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፥ ከአደጋና ከቀትር*
*ጋኔን አትፈራም።*
*በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ*
*ይወድቃሉ፤ ወደ አንተ ግን አይቀርብም።”*
*(መዝ. 91፡ 4-7)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመጎ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### <u>ጸሎት አስተምረን -- ከክፉ አድነን (ክፍል አስራ-አምስት)</u>

*“እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፡- ጌታ ሆይ... እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፡- ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... <u>ከክፉ አድነን</u>...” (ሉቃ. 11፡4)*

ጌታ ባስተማረን ጸሎት ውስጥ ሌላው የምንጸልየው ጉዳይ መለኮታዊ ጥበቃ ነው። በጸሎቱ ውስጥ እግዚአብሔር ከክፉ እንዲያድነን እንጸልያለን። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድንና የሚጠብቅ አምላክ ነው። በብሉይ ኪዳን እስራዔል በእግዚአብሔር የዳነ እና የሚጠበቅ ሕዝብ ነበር። ቃሉ ስለ እስራዔል ሲናገር “እስራኤል ሆይ፥ ምስጉን ነህ፤ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው?” (ዘዳ. 33፡29) ይላል። እስራዔል እግዚአብሔር በጸናች ክንድ ከፈርዖን መንጋጋ ፈልቅቆ ያዳነው ሕዝብ ነው። እስራዔል በማይተኛው በማያንቀላፋው አምላክ የሚጠበቅ ሕዝብ ነው። እንዲሁም በአዲስ ኪዳን እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመንን ሁሉ በጌታ ከኃጢያት የዳንን ሕዝቦች ነን። (“እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።” ማቴ. 1፡21) እግዚአብሔር ከሚጠሉንና ከወደረኞቻችን አድኖ ነው ሕዝቡና አገልጋዮቹ ያደረገን። (“ማዳኑም ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው።” ሉቃ. 1፡71)

እግዚአብሔር ደግሞ በየእለቱ በዙሪያችን ካሉ የክፉ ፍላጻዎች ሁሉ ይጠብቀናል። ስለዚህም ጥበቃ እንጸልያለን፣ እናመሰግናለንም። በመዝሙር 91 ላይ እንደምናነበው በቀኑ ውስጥ ብዙ ክፉት አለ። በቀኑ ውስጥ የአዳኝ ወጥመድ አለ፣ የሚያስደነግጥ ነገር አለ። በቀኑ ውስጥ የሌሊት ግርማ፣ የሚበር ፍላጻ፣ በጨለማ የሚሄድ ክፉ ነገር፣ አደጋ፣ የቀትር ጋኔን አለ። በቀኑ ውስጥ ተኩላ፣ ዘንዶ፣ እባብ አለ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እግዚአብሔር በክንፎቹ ጥላ የሚያድሩትን እና በርሱ የሚታመኑትን ይጠብቃቸዋል። ክፉ ነገር ወደ እነርሱ አይቀርብም። ለምን? ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ የተነሳ። ስለዚህ ወገኖቼ ከክፉ አድነን ብለን ስንጸልይ ክንፎችህ በኛ ላይ ይዘርጉ ማለታችን ነው። እርሱን ተስፋና መጠጊያ ማድረጋችን ነው። በልዑል መጠጊያ መኖራችን ነው። እርሱን መታመኛና መሸሸጊያ ማድረጋችን ነው። ያን ጊዜ እርሱ ይከበናል፣ ይጋርደናል። በአጠገባችን ሺ፣ በቀኛችንም አስር ሺ ቢወድቅም ወደኛ ግን አይቀርብም።

ወገኖቼ፡- እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? እርሱ በዙሪያችን አጥር ከሆነልን ማን ያገኘናል? እርሱ ከወደደን ምን ያሰጋናል? ዘማሪው እንደ ዘመረው ወዶናልና አዳነን። ወደ ሰፊ ስፍራም አወጣን። የምናመልከው አምላክ የሚያድን አምላክ ነው። እርሱ ከሚፋጅ እሳት ያድናል። እርሱ ከወጥመድ ያድናል። በየቀኑ ከብዙ ከምናውቃቸውና ከማናውቃቸው የክፉት ፍላጻዎች አድኖናል። ወደፊትም ደግሞ ያድነናል። የኛ መታመኛ የእርሱ ጥበቃ፣ የእርሱ እጅ ነው እንጂ የኛ ብልሃት አይደለም። በእርሱ ካለን ማንም እውሬ ከእጁ ሊነጥቀን አይችልም። እርሱ የበጎች ታላቅ እረኛ ነው። እርሱ የማይተኛ፣ የማያንቀላፋ፣ ኃይሉ የማይደክም ብርቱ እረኛ ነው። አባታችን ሆይ ከክፉ አድነን። አሜን!